የሰ/መ/ቁ 62162
ሕዳር 21 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሓጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፣ መትከል ልምዓት ሁለገብ መ/ህ/ስ ማህበር

ተጠሪዎች፣ ቄስ ካላዩ ኪሮስ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በብድር የተሰጠን ገንዘብ ይመለስ በሚል የቀረበውን ክስ የሚመለከት ነው፡፡ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የስሃርቲሳምሬ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን የከሰሰው ታህሳስ 15 ቀን 1997 ዓ.ም. የውሃ ሞተር ዋጋው 4900.00(አራት ሺኅ ዘጠኝ መቶ ብር) በ9% ወለድ ስሌት ለአራት አመት ጊዜ ከፍለው እንዲጨርሱ ፣ጊዜው ካለፈ ግን በ18% ወለድ ስሌት እንዲከፍል በአይነት በብድር ውል የሰጣቸው መሆኑን፣ተጠሪ በጊዜው ሊከፍለው ያለመቻሉን ገልጾ ተጠሪ ዋናውን ገንዘብ ብር 4900.00 በ9% ብር 1764.00፣ጊዜው በማለፉ ደግሞ በ18% ወለድ ብር 1499 በጠቅላላው ብር 8163.00(ስምንት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ብር) እንዲከፍለው ይወሰን ዘንድ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም ውሉ ስለመኖሩና የመክፍያ ጊዜው ስለማለፉ አምነው ወለዱን በተመለከተ ግን አስተያየት እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤትም ተጠሪን ለገንዘቡ ያለመመለስ ኃላፊ አድርጎ የኃላፊነታቸውን መጠን ግን ዋናው ገንዘብ በ9% ወለድ ታስቦ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡ በዚኅ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታውን ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የወለድ መጠኑ 18% መሆን ሲገባው የበታች ፍርድ ቤቶች 9% ብቻ በማለት የወሰኑት የፌዴራሉን አዋጅ ቁጥር 147/1991፣402/1996 እና በክልሉን አዋጅ ቁጥር 145/2000 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ተጠሪ ዋናውን የብድር ገንዘብ ከ9% ወለድ ጋር ብቻ እንዲከፍሉ በበታች ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀፅ 34(2) እና አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 5 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ለክርክሩ መነሻ የሆነው ገንዘብ ከአመልካች በውል የተበደሩት ገንዘቡ በአራት አመታት ውስጥ የሚመለስ ሁኖ በዚህ ጊዜ የሚታሰብ የወለድ መጠን 9%፣ጊዜው ካለፈ ደግሞ ወለዱ 18% እንደሚሆን መስማማታቸውን የብድር ውሉ የሚያረጋግጠው ጉዳይ ሲሆን ተጠሪም ይህንኑ ስምምነት የሚክዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የወለድ መጠኑ 9% እንዲሆን የወሰኑት አመልካች አግባብነት ያላቸውን የማህበራት ሕጎችን መሰረት አድርጎ ክርክሩን አቅርቦ እያለ በማለፍ ነው፡፡

በመሰረቱ በሕግ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሕግን ያህል አስገዳጅነት ያላቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡አንድ ውል ሕጋዊ ነው ለማለት ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678 ስር የተመለከቱትን የውል አቋሞችን ማሟላት ይገባዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሚፀና ውል ነው ለማለት የሚቻለው ውል ለመዋዋል ችሎታ ባላቸው ሰዎች መካከል ጉድለት የሌለው ስምምነት መኖር፣በቂ የሆነ እግጠኛነት ያለው የሚቻልና ሕጋዊ የሆነ ጉዳይ እና በሕጉ የሚፈለገው የውሉ አፃጻፍ ፎርም መሟላት አለባቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አከራካሪው ነጥብ የወለድ መጠኑ 18% ሊሆን ይገባል ተብሎ በአመልካች የተጠየቀው ዳኝነት ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ነው፡፡አመልካች ይህንኑ የዳኝነት ጥያቂ ሕጋዊ ነው በማለት በዋቢነት የሚጠቀሰው የማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) እና አዋጅ ቁጥር 402/1996 አንቀጽ 5 እንዲሁም የክልሉን የማህበራት አዋጅ ቁጥር 145/2000ን ነው፡፡

በበኩላችን እንደአየነው በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) ስር አንድ ማህበር ላበደረው ገንዘብ የሚያገኘው ወለድ ከባንክ የማበደሪያ ወለድ ሊበልጥ አይችልም በሚል በሃይለ ቃል የተቀመጠ የነበረ ሲሆን ይህንኑ አዋጅ ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 402/1996 ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 34(2) ስር ተቀምጦ የነበረው ድንጋጌ ሙሉ በሙሉ መሻሩን በአንቀጽ 5 ስር አስፍሯል፡፡ እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 147/1991ን ለማስፀፈም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 106/1996 በአንቀጽ 11 እና 14 ድንጋጌዎች ስር ከአስቀመጣቸው ሁኔታዎች የብድር አሰጣጥ ስርኣት በማህበሩ መተዳደሪደያ ደንብ ሊወሰን እንደሚችል መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ የማህበራት አዋጅ ቁጥር 145/2000ም ተመሳሳይ ይዘት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሕጉ ረገድ ያለው ማዕቀፍ ይህን የሚመስል ከሆነ አመልካች ከተጠሪ የ18% ወልድ ጥያቄ ያቀረበው በሕጉ አግባብ የተመሰረተው መተዳደሪያ ደንብ የሚፈቅድ መሆኑንና ይህንኑም ተጠሪ አውቀው ግዴታ የገቡ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ከተጠሪ 18% ወለድ የማይጠይቅበት እና ተጠሪም በገቡት ግዴታ መሰረት የማይወጡበት ወይም 18% ወለድ የማይከፍሉበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በዋናው ገንዘብ 9% ወለድ ብቻ ነው ሊከፍሉ የሚገባው በማለት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በሰሃርቲሳምሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 004448 ግንቦት 12 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡባዊ ምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 02682 ግንቦት 26 ቀን 2002 ዓ.ም. እንዲሁም በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 40515 መስከረም 21 ቀን 2003 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. ከአመልካች ጋር በተደረገው የብድር ውል ተጠሪ የብድር ጊዜው ካለፈ በሁዋላ የሚታሰበው ወለድ 18% ነው ብለናል፡፡በዚህም መሰረት ተጠሪ በጠቅላላው ለአመልካች ብር 8163.00(ስምንት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ብር) ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት